# ልትድን ትወዳለህን?

በዚህ ዓምድ **ወጣቱ ትውልድ** ራሱን ከዘመኑ ቀሳፊ በሽታ እንዴት መከላከልና ሌላውን በምን መልኩ ማስተማር እንዳለበት የሚገልጹ መጽሐፍ ቅዱሳዊና ጥናታዊ ጽሑፎች፣ቃለ መጠይቆች፣ ግጥሞች ወዘተ. ይቀርቡበታል::

## ሰዎች እንዲሠቃዩ እግዚአብሔር ይፈቅዳልን?

መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

እግዚአብሔር መሐሪና ርኅሩኅ ስለ ሆነ የሰው ልጅ በጤናማ ሕይወት እንዲኖር እንጂ በሕማምና በሥቃይ የተሞላ ሕይወትን እንዲኖር አይሻም፣ ደስታውን እንጂ መከራውንና ኀዘኑን ጭንቀቱንም አይፈቅድም።

በመጀመሪያ እግዚአብሔር:- ሰውን ከሕማምና ከሥቃይ ከኀዘንም ከሞትም ነፃ አድርጎ ፈጥሮት ነበር። ይህንም እውነት እንደሚከተለው ከብሉይ ኪዳን እንመለከታለን። «እግዚአብሔር ሞትን አልፈጠረም፤ የሰዎች ጥፋትም አያስደስተውም፤ ሕያው ሆኖ ይኖር ዘንድ ሰውን ፈጠረ፣ የዓለም ተፈጥሮም ለሕይወት ነበረ፣ በውስጡም የጥፋት መርዝ (በሽታ) አልነበረም።...ነገር ግን ሰዎች ራሳቸው ሞትን በእጃቸው በቃላቸውም ጠሩት፣ ወዳጅም አስመሰሉት ጠፉም...» (ጥበበ ሰላሞን ፩፥፲፫–፲፮)

የሰው ልጅ ስለ ሕይወቱ የተሰጠውን የሕይወት መመሪያና ትእዛዝ በመተላለፍ ራሱን በራሱ ለድካም ለሕማምና ለሞት ዳርጓል። በተድላ በደስታ እንዲኖርባት፣ እንዲጠብቃትና እንዲንከባከባት የተሰጠችውንም ምድር እንድትረገምና በጭንቅ እንድትሞላ አድርጓል።

ይሁን እንጂ ሰው:- እግዚአብሔርን ቢረሳ እግዚአብሔር ሰውን አልረሳውም፤ ሰው ከእግዚአብሔር ሸሽቶ ለመደበቅ ቢሞክር እግዚአብሔር ፈለገው። በተሰጠው ሕሊና ሊጠቀም ባይችል የጽሑፍ ሕግን ሠራለት። ይህም የብሉይ ኪዳን የመጀመሪያው ክፍል ነው። እግዚአብሔር በዚህ የብሉይ ኪዳን መጀመሪያ ክፍል የሰዎችን ጤንነት በተመለከተ በርካታ መመሪያዎችንና ማስጠንቀቂያዎችን ሰጥቷል፤ ለምሳሌ:-

፩. ከእንስሳት መካከል ንጹሕ የሆነውን ብቻ እንዲመገቡ (ዘሌ.፲፩፥፳–፳፬)

፪. ከሰው አካል የሚወጣ ማናቸውም ፈሳሽ የሚነካውን ማናቸውንም ልብስ ምንጣፍና ዕቃ በውሃ ማጠብ፣ ወይም በእሳት ማቃጠል፣ ወይም መስበር እንደሚገባ (ዘሌ.፲፫፥፵፮–፶፪)

፫. ሰፈራቸውን ሁሉ በንጽሕና መጠበቅ እንደሚያስፈልግ (ዘዳ.፳፫፥፲፬)

፬. በዝሙት ጠንቅ ከሚመጣው ከማናቸውም ደዌ እንዲጠበቁ፣ የባልና ሚስት ፍቅር እንዲጸናና ማኅበራዊ ኑሮ እንዳይበላሽ «አታመንዝር» በማለት ሕግ ሠራላቸው። አብዛኛውን ጊዜ የዝሙት ሥራ ሊስፋፋ የሚችለው ወንዶች ያለ ሚስት፣ ሴቶች ያለ ባል ሲኖሩ ስለ ሆነ ፈት ወንድና ፈት ሴት በኅብረተሰቡ መካከል መገኘት እንደ ሌለባቸው አዘዘ። (ዘዳ.፳፫፥፲፯)


ይህንም ሁሉ የሚያስፈጽሙ ካህናትና ነቢያትን ሾመላቸው።

ካህናት እንደ ነቢያት ልዩ ጥሪንና መልእክትን የማይጠብቁ የኅብረተሰቡ አገልጋዮች በመሆናቸው በየቀኑ የሕዝቡ አስተማሪዎችና አማካሪዎች፣ ጸሎትና መሥዋዕትንም ወደ እግዚአብሔር አቅራቢዎች ነበሩ፤ መቅሠፍት በሕዝቡ ላይ ሲመጣ እግዚአብሔር መቅሠፍቱን እንዲያርቅ ጾምና ምሕላን የሚያውጁ ነበሩ። ይልቁንም እንደ ጤና ባለሙያ ለበሽተኞች ምርመራ የሚያደርጉ እነርሱ ነበሩ፤ ይህንም በዘሌ.፲፫፥፲፬ ምዕራፎች እናያለን።

እነዚህ ምዕራፎች:- በተለያየ የቆዳ በሽታ የተያዙ ሰዎች በሽታውን ወደ ጤናማዎቹ እንዳያጋቡ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚያስፈልጋቸው፣ ካህናትም ለበሽተኞች ልዩ ክትትል እንዲያደርጉላቸው የሚያመለክቱ ናቸው። በምዕራፍ ፲፫፥፩–፵፮ በቆዳ ላይ ከሚወጡት አስከፊ በሽታዎች አንዱ ለምጽ እጅግ አሰቃቂና በሽተኛውን እንደ ርኩስ የሚያስቆጥር ከኅብረተሰቡም የሚያስገልል እንደነበረ ተገልጦአል።

በብሉይ ኪዳን ዘመን በቆዳው ላይ አንድ ዓይነት በሽታ የታየበት ሰው ወደ ካህኑ ቀርቦ በሽታው ለምጽ ወይም ሌላ ደዌ መሆኑና አለመሆኑ ማስመርመር ግዴታ ነበረበት። በቆዳው ላይ የወጣው በሽታ ለምጽ መሆኑና አለመሆኑ እስኪታወቅ ከታወቀም በኋላ የሚድን ከሆነ እስኪድን ድረስ በሽተኛው ከኅብረተሰቡ ተለይቶ፣ ከሰፈር ወጥቶ፣ ይቆይ ነበር።

በለምጽ ደዌ የተያዘው ሰው ጤናማዎቹ እንዳይቀርቡት ራሱ ማስጠንቀቅ ነበረበት «ልብሱን ቀድዶ፣ ክንብንቡን ከራሱ አውርዶ፣ ከንፈሩን ጋርዶ ‹አትቅረቡኝ› እያለ ይናገራል» (ዘሌ.፲፫፥፵፭)። የለምጽ ደዌ የበሽተኛውን አካል በሙሉ ካዳረሰው ሰውየው ንጹሕ መሆኑ በአደባባይ ይነገርለታል።



«ለምጹ በቁርበቱ ላይ ሰፍቶ ቢወጣ ለምጹ የታመመውን ሰው ቁርበቱን ሁሉ ከራሱ እስከ እግሩ ድረስ እንደ ሸፈነው ለካህኑ ቢመስለው ካህኑ ይመለከታል፤ ለምጹ ሥጋውን ሁሉ ቢሸፍነው የታመመውን ሰው ንጹሕ ነው ይለዋል፣ ሥጋው ሁሉ ፈጽሞ ተለውጦ ነጭ ሆኖአልና ንጹሕ ነው» (ዘሌ.፲፫፥፲፪–፲፫)

ከዚህ በላይ እግዚአብሔር ለሁለቱም ወገኖች ማለት ለበሽተኛውና ለጤነኞች እንደሚጠነቀቅላቸው እና ያለን። በሽተኛው ፈውስ እስኪያገኝ በገለልተኛ ቦታ እንዲቆይ መደረጉ በአንድ በኩል ለበሽተኛው ልዩ ርዳታ፣ ጥበቃና እንክብካቤ ሊደረግለት የሚገባ መሆኑን ያሳያል፣ በሌላ በኩል ደግሞ በሽታው የሚጋባ ከሆነ ወደ ሌሎች እንዳይተላለፍ መጠንቀቅን ያመለክታል።

በ፪ኛ ነገሥት ፭፥፲ እና በዘኁልቁ ፲፪፥፮–፲ ላይ እንደምንመለከተው ለምጽ በእግዚአብሔር ኃይልና ተአምር ካልሆነ በቀር ፈዋሽ መድኃኒት ያለው መሆኑ አልተገለጠም። ሆኖም እግዚአብሔር የማይፈውሰው ደዌ የማያሸንፈው ኃይል ሊኖር ስለማይችል የሚሳነውም አንዳች ነገር ባለመኖሩ በፈቀደ ጊዜ በሽተኞችን ይፈውሳቸዋል። ሥቃያቸውን ሁሉ ያስወግድላቸዋል። በበሽታቸው ምክንያት በኅብረተሰቡ ዘንድ መጠላታቸውን መነቀፋቸውንና መናቃቸውን ሁሉ ያስወግድላቸዋል።

በጠቅላላ ከብሉይ ኪዳን ክፍል እንደምንረዳው በለምጽም ሆነ በሌላ ደዌ ለተያዙት ሁሉ የቅርብ ጠያቂዎች፣ አጽናኚዎችና አማካሪዎች ካህናት ነበሩ። ሌላው ኅብረተሰብእ ሲርቃቸው የሚቀርቧቸው ካህናት ነበሩ፤ በሽተኞችን ከጤናማዎች ለይተው ለበሽተኞች የሚጸልዩ መሥዋዕታቸውንም ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርቡላቸው የእግዚአብሔርንም ይቅርታ የሚያበሥሩአቸው ካህናት እንዳነበሩ ግልጽ ነው። (ዘኁል.፲፯፥፴፯–፶)። ጤናማው ኅብረሰብም በማናቸውም አይነት በሽታ እንዳይለከፍ ማስጠንቀቂያ የሚሰጡ እነዚያው ካህናት ነበሩ።

እነሆ ለብሉይ ኪዳን ካህናት የተሰጠው ኃላፊነት ሁሉ የዛሬዎችን ካህናት ይመለከተናል። በክርስትና እምነት ሁሌም ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን ናቸው። በሽተኞችም ጤናማዎችም ለእኛ እኩል ናቸው። በሽታቸውን እንጂ እነርሱን ልንጠላቸው አይገባም። ለኤድስ ሕሙማን አስፈላጊውን አገልግሎት መስጠት ተገቢያችን ነው። ኤድስ በማወቅም ባለማወቅም፣ በስህተትም በድፍረትም ሰዎችን ሊይዛቸው ስለሚችል ከመተቸት ከመመጻደቅ ከመሣለቅ፣ በሽተኞችን አንጓጦ ከመመልከት፣ ከሌላው ኅብረተሰብ ተለይተው ይቅርታ የማይገባቸው፣ እግዚአብሔር የረገማቸው ኃጢአተኞች እንደሆኑ አድርገን እንዳንመለከታቸው ማሰብና ይህንም ለሌሎች ማሳወቅ የካህንነታችን ዓላማ መሆኑን መገንዘብ አስፈላጊ ነው። እርግጥ በሽተኞችን ነፃ ናችሁ፣ ወይም በሽታችሁ ይህ አይነት በሽታ ነው ለማለት አንችልም። የእኛ ድርሻ ማስጠንቀቅ፣ መምከርና ማስተማር፣ ማጽናናትም ነው።

ተላላፊ ደዌ ያለበት ሰው:- በሽተኛ መሆኑን ገልጦ መናገር እንዳለበት በዘሌዋውያን ፲፫፥፵፭ ላይ ተመልክተናል። ይህም ለባልንጀራ ፍቅርና ርኅራኄን ማድረግ ማለት ነው። በሽታው በራስ ብቻ እንዲያበቃ ሌላው በተመሳሳይ በሽታ እንዳይጠቃ ለማድረግ መጠንቀቅና ማስጠንቀቅ ታላቅ ፍቅር ነው። ከዚህም የበለጠ ፍቅር አይኖርም። በሽታውን መዋጋትና መከላከልም ማለት ይህ ነው። ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ያለባቸው ሁሉ ይህን አይነት ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል። «ጉድ አያት የእኔም ጉምድ» እንዳለው ሰዉ መሆን አያስፈልግም። በቀል ማድረግ ተገቢ አይደለም። ወንዶች ሴቶችን፣ ሴቶችም ወንዶችን መበቀል ፍጹም ኢ ሰብአዊነት ስለ ሆነ «እግዚአብሔር በቀል የእኔ ነው ይላልና አትበቀሉ» የሚለውን ቃል አጥብቀን ልናስተምር ለእኛ ለካህናት ግዴታችን ነው።

በኦሪት ዘዳግም ውስጥ እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ቃል ቢሰሙ ያዘዛቸውንም ትእዛዝ ሁሉ ቢጠብቁ ሕይወታቸውንና ለሕይወታቸው አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ሁሉ የሚመለከት የተትረፈረፈ በረከትን እንደሚያገኙ ተነግሮአል።

በተቃራኒው ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃል ባይሰሙ ያዘዛቸውንም ሥርዐቱንና ትእዛዙን ባይጠብቁ ባያደርጉም ሕይወታቸውንና ለሕይወታቸው አስፈላጊ የሆኑት ነገሮች ሁሉ የሚነኩ የተለያዩ መቅሠፍቶችና በገ
ታዎች እንደሚደርሱባቸው ተዘርዝር
ተገልጦአል።

በዚህም ክፍል የተዘረዘሩት የ
ሽታ አይነቶች የሚከተሉት ናቸው።

- ቸነፈር፣ ክሳት፣ ንዳድ፣ ጥብሳት ትኩሳት (ቁ.፳፩–፳፪)
- ፈውስ የሌለው ቁስል፣ ዕባጭ
  ቋቁቻ፣ ችፌ፣ ዕብደት፣ ዕውርነ
  (ቁጥር ፳፯–፳፰)
- ለብዙ ዘመን የሚቆይ ደዌ፣ በዘ
  መጽሐፍ ውስጥ ያልተጠቀሰ ለ
  ደዌ፣ የልብ መንቀጥቀጥ (ቁ.፶፱–፳

እነዚህ በሽታዎች ሁሉ በሕዝቡ ሊመጡ የሚችሉ መሆናቸውን እግዚ አብሔር እንደ ተናገረ ስንሰማ ጨካ ኝና ለፍጥረቱ ርኅራኄ የሌለው አም ላክ እንደ ሆነ የሚሰማን እንኖር ይሆ ናል። ነገር ግን ድርስ ነገሩ እንደዚህ አይደለም።

በዘዳግም ፳፰ ውስጥ የተጠቀሱት በረከቶችና መርገሞች ጤናዎችና በሽ ታዎች፣ ሕይወትና ሞት በሰዎች ላይ የሚከሰቱት በእግዚአብሔር ጭካኔና ምሕረት የለሽነት ሳይሆን በሕዝቡ ምርጫና ፈቃድ መሆኑ በዚሁ መጽ ሐፍ በምዕራፍ ፴ ውስጥ በሚገባ ተብራርቶ ተነግሮአል።

«በፊታችሁ ሕይወትንና ሞትን፣ በረከትንና መርገምን፣ ክፋትንና መል ካምነትን አኑሬአለሁ እንግዲህ:- አንተና ዘርህ በሕይወት ትኖሩ ዘንድ ሕይወትን ምረጥ፣ የሕይወትህና የዘ መንህ ርዝመት ራሱ እግዚአብሔር ነውና እግዚአብሔርን ለመውደድ፣ ቃሉንም ለመስማት ምረጥ።» (ዘዳ. ፴፥፲፭–፳)

ከዚህ ላይ ሁለት መንገዶች ብቻ እንዳሉ ይታያል። እነርሱም አንዱ የሕይወት ሁለተኛው የሞት መንገዶች ናቸው። በሁለቱም መንገዶች ለመጓዝ ምርጫው የእያንዳንዱ ሰው ነው። እግዚአብሔር እኛ ራሳችን ምርጫ እንድናደርግ ይፈልጋል። ሞትና ሕይ ወት በእግዚአብሔር እጅ ውስጥ ያሉ ቢሆንም ሰውም ስለ ሕይወቱና ስለ ሞቱ የራሱ የሆነ የኃላፊነት ድርሻ አለው። ነፃ ፈቃድ አለው።

በዘዳግም ፳፰ በተሰጠው ማስጠ ንቀቂያ መሠረት ዛሬም ሞትና ሕይ ወት በፊታችን ለምርጫ ቀርበዋል። ከሞት ይልቅ ሕይወትን መምረጡ የእኛ ፈንታ ነው። ሕይወትንም መም ረጥ የምንችለው ከዘዳግም ፳፰፥፲፱ እንደምንረዳው:- እግዚአብሔርን በመውደድ ነው፤ ቃሉን በመስማት ነው፤ ትእዛዙንም በመጠበቅ ነው።

እነሆ ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ የሞት መንገድ ሆኖ በዓለም ውስጥ ከዳር እስከ ዳር ተዘርግቷል። ሰዎች እያወ ቁም ሳያውቁም በዚህ መንገድ ይጓዛሉ።

የኤድስ ምክንያቶች ብዙዎች እንደ ሆኑ በዐዋቂዎች ቢነገርም ዋና ውና አውራው ምክንያት ግን ከተፈ ቀደው ሕጋዊ ሩካቤ ውጭ የሚፈጸም ኢ ሕጋዊ ሩካቤ ማለት:-

- አንድ ወንድ በአንዲት ሴት፣ አን ዲት ሴት በአንድ ወንድ አለመወሰን፣
- የጋብቻን ክቡርነት በማቃለል ወን ዶችም ሆኑ ሴቶች በልቅነት መኖር፣
- ሌላም ሕገ ወጥ የሆነ ግብር መፈ ጸም (ሰዶማዊ ግብር) ነው።

ሰዎች ይህን ሁሉ እንዲያደርጉ የሚገፋፋቸው ሌላ የውጭ ኃይል ሳይ ኖርባቸው በራሳቸው ነፃ ፈቃድና ምርጫ ያደርጉታል። ይህም ሁኔታ ሕይወትን በሞት በረከትን በመርገም መለወጥን ስለሚያመለክት የሕይወት መንገድ የሆነውን:-

- የአንድ ለአንዲት ጋብቻን
- ከማናቸውም አይነት ዝሙት ለመ ራቅ «አታመንዝር» የሚለውን የእ ግዚአብሔር ትእዛዝ ላገቡና ላላ ገቡ ሁሉ ማስተማርና መምከር ማስ ጠንቀቅም ከካህናትና ስለ ኤድስ አደገኝነት ከፍተኛ ግንዛቤ ካላቸው ሁሉ ይጠበቃል።

በዘዳግም ፳፰ የተጠቀሱት በሽታ ዎች ሁሉም በሰዎች ላይ እንደ ደረሱና ሰዎቹን እንደ ጐዱ በሌላ ቦታ ተጠ ቅሰው አልተነገሩም፤ «በተለይ ፈውስ የሌለው ደዌና ለብዙ ዘመን፣ የሚቆይ» ደዌ በመባል የተጠቀሱት በሽታዎች ከኃጢአት ምሳሌነታቸው በቀር ተደጋግመው አልተወሱም። የሕዝቡ መንፈሳውያንና ሥጋውያን መሪዎች ከእግዚአብሔር የተላለፈ ውን ማስጠንቀቂያ በሚገባ ለሕዝቡ ስላስተላለፉና ሕዝቡም ስለ ተጠነቀ ቁና የተሰጠው የተነገራቸውን የእግዚ አብሔርን ትእዛዝ ስለ ፈጸሙ እንደ ሆነ ግልጥ ነው።

ዛሬም ስለ መንፈሳዊ ሕይወትና መዳን ብቻ ሳይሆን ስለ ሥጋና መንፈስ ሕይወትና መዳን የእግዚአብሔርን የሕይወት ቃል ለማስተላለፍ ኃላፊነ ትና አደራ የተጣለባቸው ካህናት በኤች አይ ቪ ኤድስ የተጠቁትን ለመ ርዳት ለመንከባከብ፣ ለማጽናናትና በየ ጊዜውም ለመጠየቅ፣ ያልተያዙት ንም ለማስጠንቀቅ ከብሉይ ኪዳን ካህ ናት ምሳሌን ሊወስዱ ያስፈልጋል። ❖

## ማደሪያ

ለወፍ – ጐጆ

ለዝንጀሮ – ገደል

ለቀበሮ – ጉድጓድ

ላንበሳ – ዋሻ

ለምስጥ – ኩይሳ

ለጉንዳን – አፈር

ለበግ – ጉረኖ

ላህያ – ግርግም

ለበቅሎ – ጋጥ

ለዶሮ – ቆጥ

ለእባብ – ካብ

ለከብት – በረት

ለሰው – ቤት

ለክርስቶስ – መቅደስ

ያስፈልገዋል!

እሱ ግን በትሕትና

«ሁሉ እያለው ራሱን ባዶ አደረገ»

ዲ/ን ዘመድሁን አበበ መ/ር